# ዶሮና ባቄላ

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)

መቼም በአገራችን ሜዳ ላይ በሰፊው የተዘረጉትን ገበያዎች የማያውቅ ጦቢያዊ በርካታ ይሆናል ብዬ አልገምትም። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ገበያዎች ጉብ ጉብ ካለ ሥፍራ ላይ ይመሰረቱና ሰኞ ገበያ፣ ማክሰኝት ገበያ፣ ሮቡ ገበያ፣ ሐሙሲት ገበያ፣ አርብ ገበያ፣ ቅዳምን ገበያ የሚባል ስም ይሰጣቸዋል። የናንተን አላውቅም እኔ ግን እምብዛም ሰምቼ እማላውቀው እሑድ ተብሎ የሚጠራ ገበያ መኖሩን ነው። ለምእራባውያን ገበያዎች ወለላቸው እብነ-በረድ ወይም የተሸቆጠቆጠ ስጋጃ፣ ላዩም በተካኑ የሰው ልጅ ጥበቦች ተውቦ የተሰራ የሚያምር አብለጭላጭ ጣራ ነው። ለጦቢያ የሜዳ ገበያ ግን ወለሉ እግዚያብሔር የሰራው አፈርና ጠጠር፣ ጣራውም ኖህ ፍጡራን ለዘር ካተረፈው መርከቡ ውስጥ አየሩን ፈትሽ ብሎ እንደላካት እርግብ የማይዝል ክንፉን ዘርግቶ ክፉውንም ደጉንም ወደ ታች ሲመለከት የሚውል ሰማይ ነው።

“አንተም ድርድርህን ይዘህ ትጎለት ነበር ወይ?” የሚል ጥያቄ አትወርውሩብኝ እንጂ እኔ ትዝ እንደሚለኝ እንደነዚህ አይነት ገበያዎች ላይ በመጀመርያ የሚመጡት፣ እንደ ዝሃ፣ ሳሙና፣ የራስ ማሰሪያ ሻሽ(ባውንድ)፣ሻማ፣ ጧፍ  ወዘተ የመሳሰሉትን ሸቀጣ ሸቀጦች የሚይዙ ነጋዴዎች ናቸው። ከሩቅ አይን የሚስቡ አብለጭላጭ የራስ ማሰሬዎችን፣ ከነቲራዎችን፣ ቀለማም ዝሃዎችን ወይም ሌላ አይነት ቦግ ቦግ ብለው የሚታዩ ጨርቃጨርቆችን በእንጨት አንጠልጥለው ከገበያው እምብርት ላይ እያወዛወዙ የገበያ መልክና ውበት ያርከፈክፉበታል። በማከታተልም ቅርንፉድ፣ ዘቃቅቤ፣ ድንብላል፣ ዝንጅብል፣ ሰናፍጭ፣ ሽንኩርት፣ ጌሾ፣ ኮሰረት፣ በርበሬ ወዘተ የመሳሰሉትን ቅመማቅመሞች ከቅርጫት ሆድ ወይም ከአቆማዳ ጉንጭ ውስጥ እያወጡ የሚደረድሩ ወይዛዝርትና ጎበዛዝት ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይቀመጣሉ። በአህያ ወይም በአጋሰስ ጀርባ ላይ ተንፈላሶ የመጣ የጤፍ፣ የስንዴ፣ የሽንብራ፣ የባቄላ፣ የአተር፣ ወተርፊ አቆማዳና ጆንያማ የጦቢያ ገበያ የጀርባ አጥንቱና መለያ ባህሪው  ነው።

የጊዜ ጉዳይ ስለሚገደበኝ እንጂ በእውነቱ  ስለገበያ ሳወራ ውዬ ሳወራ ባድር ይደክመኛል ብዬ አላስብም። አዎ በገበያ ጎልማሳ አዛውንቱ ያደለበውን በሬ፣ ያሳደገውን ጠቦት ወይም የቀጠቀጠውን ሙክት ከብት- ተራ አቁሞ በኩራት ነጠላውን አፍንጫው ላይ ጥሎ ከዘራ ወይም ዱላውን ተመርኩዞ ገዥን ሲጠባበቅ ያስተውላሉ። ገዥም ገንዘቡን መጀመሪያ ባለመቶ፣ ከዚያም ባለሃምሳ፣ ባለ አስር፣ ባለአምስትና አንድ ብር ኖቱን መስመር መስመር አሲዞና አጣጥፎ በክር ወጥሮ አስሮ በቀላሉ ሊደረስበት ከማይችል የአካሉ ክፍል ጋር ደብቆ የሚገዛውን ከበት ሲያማርጥ ይመለከታሉ። ይህም ብቻ አይደለም። ገበያ ሴቶቹ ተኳኩለውና አጊጠው እድላቸውን የሚፈትሹበት፣ ወንዶችም ጥርሳቸውን እየፋቁ የሚጥልላቸውን እጣ ፈንታ የሚጠባበቁበት የመተጫጫ ቦታም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ገበያ ጦር ሜዳ ይመስል በሴት የተጣሉ ወንዶች በዱላ ሲከሳከሱ፣ ወንድ የተቀማሙ ሴቶችም በጥፊ ሲላላፉ ይታያሉ። ታዲያ ከሁሉም የገበያ ድንቅ ገጽታዎች ግን እኔን ውሃ እንደጠማው ሰው የሚያረካኝ ገበያ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ጾታ ወዘተ ሳይል ሁሉንም የሚቀበልና የሚያስተናግድ፤ እንኳን የሰው ልጅ ሌሎችም የህል ዘሮችን ጨምሮ አናሳ ፍጡራን የሚገናኙበት ቦታ መሆኑ ነው። የገበያ ትርጉም፣ የገበያ ውበት፣ የገበያ በረከት እንኳን እንደኔ ዶማ ኮቢ ብቻ ይዞ፣ እንደነመምሬ ቀረ-በከንቱ አፈ-ከርፋፋ ጽዋ ጨብጦም የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም። ለማንኛውም ዛሬ እስቲ ስለ ዶሮ-ተራ ታሪክ የማስታውሰውን አንድ ሁለት ልበል።

እንደምታውቁት ዘመናዊ የዶሮ እርባታ በአገራችን ብዙም የተለመደ አይደለም። ዶሮን የሚያረባው አብዛኛውን ጊዜ ያው ከአለም በፊት ተፈጥሮ ውራ ላይ የሚገኘው፣ እያመረተ የማይበላው አፈር ገፊው የጦቢያ ገበሬ ነው። አውላላ ሜዳ ላይ ከሚገኙት ገበያዎች ውስጥ እየለቀመ የሚገዛው ደግሞ ትከሻው ላይ በሚጋደም አጣና ወይም ዱላ ዳርና ዳር ላይ ዶሮን ዘቅዝቆ አስሮ  እያፋጫጨ የሚነጉድ ነጋዴ ነው። ታዲያ መለስተኛ ሁለተኛ ደርጃና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረዳ ት/ቤት እያለሁ በዚህ መልክ የሚነግዱ የሰፈሬና የትምህርት ቤቴ ልጆች ነበሩ። እንደ አቅሚቲ የንግድ ባለሙያ እንደመሆናቸው መጠን እነዚህ ልጆች ትምህርት ቤት ስንገናኝ ስለ ዶሮ ንግድ ሙያና ጥበብ ያወሱን ነበር። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ብዙን ጊዜ የሚያጫውተን ዶሮን ገበያ ውስጥ እንዴት አታሎ መውሰድ እንደሚቻል ነበር።። ነገር ግን “ዶሮን ሲያታሏት በመጫኛ ጣልዋት” የሚባለውን ተረት በማስታወስ ይህ ተንኮለኛ መጫኛ እየጎተተ ወደ ዶሮ ተራ የሄደ እንዳይመስላችሁ።

ይህ “ጎበዝ” ስለዶሮ የመስረቅ ችሎታው ሲያወሳን በጀብዱነት መንፈስ ተውጦ ነበር። አዎ ይህ “ሳተና” ለዚህ ተግባር ሲሰማራ መጀመሪያ በውሃ ተነክሮ ያደረ ባቄላ በኪሱ ይዞ ወደ ገበያ ይሄዳል። ዶሮን ከስንዴ ጋር በቅርጫት ተሸክመው ገበያ ያመጡ ወይዛዝርት ወሬ ለወሬ ተቆላልፈው፣ ስለ ወይዘሮ ማንትስ እግረ ሽፋፋነት፣ ስለአቶ እገሌ ሱሪ ወላዳነት፣ ስለ መምህሬ አደፍርስ ሐጂነትና ሌላ ሌላውም ጉዳይ የባጡን የቆጡን ሲያወሩ ስንዴ ፈሶለት በመልቀም ላይ ያለ ዶሮ እግር ማውጣት ይጀመራል። ያን ጊዜ የዶሮን አመል በሚገባ ያጠና ይህ “ጠቢብ” ውሃ ምጎ ምጎ ያበጠውን ባቄላ በረጅም ክር

ያስርና ወደ ዶሮው ልኮ እርሱ ከገበያው ዳር ሆኖ በርቀት ይጠባባቃል። "ስንዴ በጤና" ብሎ እያመሰገነ መመገብ ያቃተው ዶሮም ስስትና ጉጉት አንጎሉን ይወረውና ወገቡ ላይ የታሰረውን ባቄላ ኩ.. ኩኩ..ሉ የሚለውን ጸሎት አድርሶ ለቀም አርጎ ይጎርሰዋል። ጉቦ ውጠ ውጠ እንዳበጠ ጉንጭ የተነፋፋ ባቄላም የዶሮውን ጉርንቦ ጥርቅም አርጎ ይዘጋና እርፍ ይላል። ባቄላም ላንቃ ላይ ተተክሎ ወይ ወደ ውስጥ አይገባ አለዚያም ወደ ዉጭ አይወጣ ዶሮን ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ማሰቃየት ይጀምራል። በዚያን ወቅት በዶሮ ባህሪ ላይ የሚራቀቀው ጣፎርዴ ነጋዴ ክሩን መጎተት ይጀምራል። በጉርሻ የተያዘ ዶሮም አማራጭ ያጣና ባቄላው የታሰረበትን ክር ተከትሎ ከኪስ አውላቂ እጅ ውስጥ ሰተት ብሎ ገብቶ ያርፈዋል።

ድሮ በዳቦ ቅርጫትነት ዛሬ ደግሞ በችጋር ምንጭነት የሚታወቀው አበሻ ሲያወራ ይቆይና ወግን ከቁም ነገር ለማያያዝ ሲከጅለው "ላይፈቱ አይተርቱ" ይላል። ለነገሩ ከላይ የተገለጠው ጉዳይ ተረት ሳይሆን እንዲያውም አንዴ  ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ በስራ ላይ የዋለ ጉዳይ ነው። "አንተም ሳታደርጋት አልቀረህም"  ብትሉኝ የማፍር እንዳይመስላችሁ። እንኳን ዶሮ የሰረቀ፤ የሰውን ልጅ እንደ ጠቦት የሰዋና አገር የሸጠም ሲያፍር ወይም ፍርድ ቤት ሲቀርብ አልታየ። ለማንኛውም አንባቢ ሆይ! ልቡናችሁ ከዶሮ ሌባው፣ በክር ከተወጠረው ባቄላና እንደዚሁም ከስስት ማጥ ውስጥ ከሰመጠው ዶሮ ላይ ያተኩርልኝ። እንቁላል አስታቅፈው፣ ኩስ እየጠረጉ ጫጩት አሳድገው፤ በመጨረሻም ሸጠው ለመጠቀም ተሸክመው ገበያ ወስደው በከንቱ ለጭልፊት የዳረጉትን ያልታደሉ ሰዎችም አትርሱ።

ስርቆትም ከቁም ነገር ተቆጥሮ እናውራ ከተባለ ሌባን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል። አሙለጭላጭ ሌባ፣ ወንበዴ ሌባናና ኪስ-አውላቂ ሌባ የሚባሉ ስሞች ሰጥቶ ማለቴ ነው። አሙለጭላጭ ሌባ ጨለማን ወይም ጸጥታን ተገን በማድረግ የሚሰርቅ፣ ሲነቃበትም ደንግጦ የሚበር የሌባ አይነት ነው። የዚህ አይነቱ ሌባ ብዙውን ጊዜ በር ሰርስሮ፣ መስኮት ከፍቶ አንዳንዴ እንዲያውም አሙለጭልጮ ለማምለጥ እንዲመቸው ራቁት ገላውን ቅቤ ተቀብቶ የሚሰርቅ ሌባ ነው። ወንበዴ እንደሚታወቀው አናት የሚፈጠፍጥ ዱላ ወይም የብረት መሳሪያ (ጠመኝ፣ ሰንጢ፣ ቢላዋ ወዘተ) ይዞ እያስፈራራ የሚዘርፍ ከአውሬም የከፋ አደገኛ ፍጡር ነው። ብዙ ጊዜ ሰው ወንበዴንና ሽፍታን ያምታታቸዋል። ነገር ግን ወንበዴና ሽፍታ በምድር ተስማምተው አብረው የማይኖሩ፤ በሰማይም እንደ አጻጻፋቸው ቅደም ተከተል ሲኦልና ገነት የሚገቡ ፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ሽፍታ የሚሸፍተው በሕዝብ ላይ ሳይሆን በአረመኔ ሥርዓት ላይ ነው። ወንበዴ ግን የሚወነብደው ጨጓራውን ለሞሙላትና ከርሱን ለመወጠር ሲል በሕዝብ ላይ ነው። አዎ ሽፍታ ነጻ አውጭ ሲሆን ወንበዴ ግን ዘራፊና ነፍሰ-ገዳይ ነው። ኪስ-አውላቂ ሌባ በፈንታው በማምታታት ቀልብን አነሁልሎ አይን ተጉረጥርጦ እያለ ሳይቀር ንብረትን ሞጭልፎ የሚሄድ የሰው ጉድ ነው። የዶሮውን ልብ በባቄላ ያማለለው ግለሰብ ከዚህኛው ክፍል ሊመደብ ይችላል።

ጦቢያ አይሁዱ ቤተ-ምኩራቡ ውስጥ ወርቦ፣ ክርስቲያኑ ቤተ-ክርስቲያኑን ስሞ፣ እስላሙም መስጊዱ ውስጥ ጸልዮ በሰላም የሚኖርባት፤ ብሉይ ኪዳን፣ አዲስ ኪዳንና  ቁርአን ደጋግመው የሚጠቅሷት ታሪካዊ አገር ናት። እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ተፈጥሮ የአየር ንብረቷን በቴርሞ-ሜትር ለክቶና አስተካክሎ የፈጠራት ምድር ናት። እውነት ነው ጦቢያ ከማእበል እንዲተርፉ በኖህ መርከብ ላይ እንደተሳፈሩት ህዋሳት ከሁሉም የፍጡራን ዘር ተውጣጥቶ በውህደት የተዋቀረች ቅዱስ ገበያ ነበረች። ዳሩ ግን እንደ አለመታደል ይህች ገበያ አገዛዝ ከሚባል ጫካ ውስጥ ተደብቀው ሕዝብን በሚዘርፉ ወንበዴና ሌላም አይነት ሌቦች አበሳዋን ስታይ ኖራለች፤ እየኖረችም ነው። ወንበዴ ሌባ አይነ ደረቅ ነው። በጠራራ ጸሐይ እያስፈራራ ንብረት ይገፋል። ነቃሁብህ ሲሉት፣ ዝርፊያህን አቁም የሚል ትንፋሽ ሲያወጡ የፍጥኝ ያስራል፣ እንዲያም ሲል ይገላል። አሙለጭላጭ ሌባም ከጀርባ ተደብቆ በርሃብ እንደ ቅጠል ከሚረግፉ ህጻናት ጉረሮ ሳይቀር ወንበዴ ሌባ የዘረፈውን በሚስጥር፣ በስርብትናና በሙስና እየተጋራ በሐብት ይናጥጣል። በዚህ መልክ በጦቢያ ምድር የተፈጠረውን አሙለጭላጭ ሌባ ብዛት እርሱ ይቁጠረው። ይህም ብቻ አይደለም። እድሜ ለወንበዴ ኪስ- አውላቂ ሌባም እንደ አሸን ፈልቷል።

በባህልም ሆነ በታሪክ ስናውቀው ኪስ አውላቂ ሌባ ድሮ ድሮ የሚሰርቀው ከሚስጢር ኪስ ወይም ከቁርባብች(እንግዳ ለሆነባችሁ ቁርባብች ከፍየል ወይም በግ የዘር ፍሬ መሸፈኛ ቆዳ የሚሰራ የቆፍጣና ወንድ ልጅ ቦርሳ ነው) ውስጥ ያለ ሽልንግ ግፋ ቢልም ከላይ እንደተገለጸው በባቄላ የሚታለልን ዶሮ ነበር። ዛሬ ዛሬ ከአገዛዝ እሾሃማ ጫካ ውስጥ የሚላኩት ኪስ-አውላቂ ሌቦች የሚሰርቁት ግን ውሃ ምሳ ምሳ ያበጠ ባቄላን ሲያዩ ልባቸው እንደ ቅቤ ቀልጦ የሚፍረከረከውን የዶሮ ዘፋኞች፣ የዶሮ የጦር መሪዎች፣ የዶሮ ፖለቲከኞች፣ የዶሮ ምሁራን፣ የዶሮ ቀሳውስት፣ የዶሮ መነኩሳትና ሌሎችም ሞት የሚባል ነገር መኖሩን የሚረሱ ከንቱ ሰዎች ነው። (ስለሰው አይነቶች ይህችን ዋቢ* ያንብቡ።) ባቄላም በበኩሉ በስልጣን፣ በገንዘብ፣ በቤት፣ በመሬትና ሌላም ሌላም መቅቡጥ ወይም ረብ መልክ የሚከሰት ማተለያ ሆነና አረፈው።

ተፈጥሮ እንደሚለውና እንደሚያዝዘውማ ቢሆን ማንኛውም ዜጋ በተፈጠረበት ወይም አገሬ በሚለው ምድር ላይ ቤት-ሰርቶ የመኖር፣ ንብረት የማፍራት፣ ወልዶ የማሳደግ፣ ከፈለገ በየትኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ስልጣንን ተወዳድሮ የማግኘት ከምድር ብቻ ሳይሆን ከላይ ከሰማዩ የተሰጠ ያልተሸራረፍ የመብት ጸጋ አለው። ዳሩ ግን እንደ እርግማን ይሁን እንደ ቅጣት ጦቢያውያን ይህንን ሁሉ መብታቸውን አገዛዝ ጓሳ ውስጥ የተደበቀ ወንበዴ  በጠራራ ፀሐይ ዘርፏቸዋል። አሙለጭላጭና

ኪስ አውላቂ ሌባም ወንበዴውን ሌባ ደጅ እየጠና የተዘረፈውን የዶሮ ንብረት እየተጋራ ይሉኝታውን ጥሎ ሲፍነሸሽ ይታያል። በሌላ በኩል ግን ዶሮ አርቢውን ሕዝብ ሰቆቃ ጠብሳ ስትበላው እርሱም መከራን ቀቅሎ ሲበላ ይውላል።

እርግጥ ነው ኪስ-አውላቂ ሌቦች እንዲያውም ከአገርም ተሻግረው በዚህ በውጩ አለምም እየመጡ ስልጣንን፣ ብርን፣ ቤትን፣ መሬትን ወዘተ እንደዶሮ በክር እያሰሩ ወደ ሰዎች እየወረወሩ የስንቱን ልብ ባር ባር አሰኝተዋል። አረፍስሰዋልም። ስንቱን ከሙሉ ሰውነት ወደ አሙለጭላጭ ሌባነት እየቆየ ሲሄድም ወደ ወንበዴ ሌባነት ቀይረዋል። አዎ ኪስ-አውላቂ ሌባ ባቄላን በክር አስሮ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ሳይቀር እየላከ ቁጥር ስፍር የሌለውን ቆብ በአናቱ የደፋ መነኩሴ፣ ህልቁ መሳፍርት የሌለውን መስቀል በደረቱ ያንዠረገገ ቄስና ደብተራ ልብም አስኮብልሏል። እንኳን ተራውን የኔ ቢጤ ምእመን በዚህ መልክ ከሙሉ ሰውነት ወደ አሙለጭላጭ ሌባነት ከዚያም ወደ ኪስ-አውላቂና ወንበዴ ሌባነት የተቀየረውን ሌዋውያን(ካህናት) ብዛት ስድስት ቀን ሰርቶ በሰባተኛው ቀን ያረፈው አንዱ አምላክ ይቁጠረው። አበሻስ እንዲህ አይነቱን ጉድ ማየትም ሆነ ቆጥሮ መጨረስ ተስኖት ዝም ብሎ እህህ… እያለ የታመቀ አየር እየተነፈሰ ችሎት ይኖራል።

ምድር ላይ ግፍ ተቦክቶ ሲጋገር ቢውልና ቢያድርም ዘመን ከመገስገስ አንድ ቀን ተቆጥቦ አያውቅም። እናም እኛ አዲሱን ዘመን ስናጋምስ ፈረንጆች አዲስ ዘመን ሊቀበሉ ዳር ዳር እያሉ ነው። አዲስ ዘመን ሲመጣ ብዙ ሰው ብዙ ብዙ ነገር ይመኛል። በርካታ ነገሮችን ለማከናወንም ቃል ይገባል። በዚህ በያዝነው የእኛ ዘመን ዋዜማ ወቅት "**እንቁጣጣሽ ለመባባል ያብቃን!" የሚል ምኞት ተመኝቼ ነበር። ዛሬ በፈረንጆቹ አዲስ እመት ዋዜማ የምመኘው ደግሞ አምላክ ሆይ የሌባ አይነቶችን በቃህ በላቸው፣ በማይሳነው ምናብህም መልሰህ ሰው አርጋቸው የሚል ነው። አዎ እግዚአብሔርን የምለምነው የአገዛዝን ጫካ አቃጥለው፣ በውስጡ የተሰገሰገውን ወንበዴም አጽዳው፤ የባቄላ ፍሬ በገመድ አስሮ ዶሮ ለመስረቅ የሚነጉደውን ቁጥርም አመንምነው እያልኩ ነው። እውነት የሚሰማኝ ከሆነ አላህን ሌት ተቀን የምጠይቀው በባቄላ ፍሬ የሚጎመጀውን የዶሮ ልብ ጠንክር፣ በወንበዴ ወይም በኪስ አውላቂ ሌባ ንብረቱን በመዘረፍ ላይ ያለ የገበያ ሕዝብም አንድ ላይ ከትሞ ከጥቃት እንዲድን እዝለ-ህሊውን ነቃ አርገው ብዬ ነው። " ወቼው ጉድ ምርቃት በልመና!" ብላችሁ አትሳለቁብኝ እንጅ ሐሳቤን የምትጋሩ ሁሉ ልመናህን ይስማህ ብላችሁ መርቁኝ። አሜን።

*ዋቢ*

** ለመሆኑ ሰው ምንድን ነው?*
*Sew Mindinew: www.addisvoice.com/article/sew2.pdf*

*** እንቁጣጣሽ ለመባባል ያብቃን*
*http://addisvoice.com/amh/Enqutatash.pdf*
*http://www.abbaymedia.com/pdf/Amharic/Enqutatash.pdf*

*ታህሳስ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*